# <u>ሙክት አጥብቆ ሲሰባ የመታረጃ ካራውን ይታከካል</u>!

ኃይሌ መለሰ (ብ/ጄ)

የካቲት 2001

በክህደት ዓላማቸው የረከሱትና በእኩይ ግብራቸው እንደ ኖህ ዘመን ቁራ ጠቁረው የከሰሉት ወያኔወች ባሁኑ ወቅት በማድረግ ላይ ያሉት ድርጊት ሁሉ በሁለንተናዊ መልኩ ሲገመገም የመታረጃ ካራቸውን እየሳሉ፣ የመቀበሪያ ጉድጓዳቸውን እየቆፈሩና የመጥፊያ ቀናቸውን እየቆጠሩ ናቸው ከሚያሰኝ ደረጃ ላይ ደርሰዋል ቢባል ነገ ከመሆን የማይቀረውን አስቀድሞ ከመተንበይ ባለፈ በምሬት የተነገረና ተጋኖ የቀረበ ነው የሚያሰኝ አይመስለኝም። በእርግጥ ከሙክቱ የሚለዩት ሙክቱ የራሱን መታረጃ ካራ እየታከከ ዝግጁነቱን እንዲገልጽ ያደረገው ባለቤቱ አንድ ቀን ለትንሣኤ መፈሰኪያ ይሆነኛል ብሎ በእንክብካቤ ስለያዘው ነው። ኢትዮጵያዊ ክብራቸውን ለጌቶቻቸው ሸጠው ለባርነት ያደሩት ግብረ-አራዊት ግን ጌቶቻቸው ለእንክብካቤ ብለው የጋቷቸው የእናት አገር ማጥፊያ መርዝና የከፈሏቸው የቅጥረኝነት ዋጋ መጠኑ በዝቶ ስለአሰከራቸው ይኸውና የራሳችን የክህደት ሴራ በሳለው ጦር እራሳችንን እየወጋን ለማጥፋት የተዘጋጀን ስለሆንን ፈጥናችህ ተቀቡብን የሚል ጥሪ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቅርበው መልሱን እየተጠባበቁ መሆናቸውን የሚያመላክት መሆኑ ነው። ስልሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ በቀጣይ ችግር አሳጅበው ያቀረቡለትን ወቅታዊ ጥሪ ተቀብሎ በሚገባ ለማስተናገድ ያስችለው ዘንድ ተዳፍኖ ውስጥ ውስጡን እየጋመ ሲግል የኖረውን ሕዝባዊ ሰይፍ መዞ ሊያወጥውና ሞልቶ በመፍሰስ ላይ ያለውን የግፍ ጽዋ እጅግ መርሮ እስከሚያንገሸግሻቸው ድረስ እየጋተ የአመረቀዘ ቁስሉን ሊያሽረው ይገባል።

ወያኔወች የብዙሐኑን እናት አገር ለማጥፋትና ለዘመናት ተሳስቦ የኖረውን ሕዝብ እርስ በርሱ ለማፋጀት በታቀደ ዓላማ ላይ ተመስርተው 18 ዓመት ሙሉ ሲያካሂዱ የኖሩትን አረመኔዊ ድርጊት የግድ መተንተን አስፈላጊ አይመስለኝም። ሕዝቡ እራሱ የጋረጡበትን ውስብስብ ችግሮች ያደረሱበትን አስከፊ ማህበራዊ ቀውስ አጠቃሎ ሊያሳይ በሚችል አባባል የገለጸባትን አንዲት ስንኝ ብቻ መጥቀሱ በቂ ይመስለኛል፦

> “የአገራችን ችግር ምኑ ይጠየቃል፣
>
> ያለቀውም አልቆ ያለው በቁም ደቋል።”

ብሎ ገልጾታልና ነው። መልዕክቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ ደህንነቱ ምን ያህል እንደተናጋና ለንብረቱ ቀርቶ ለሕይወቱ እንኳ ዋስትና እንደሌለው በውል የሚያመለክት ነው። ስለዕውነት ለመናገር በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሀዘን ማቅ ለብሰው የማያለቅሱትና አንገታቸውን ደፍተው የማይተክዙት፣ በረሃብ ጦር ተወግተው ያልደቀቁትና በቁማቸው ያልጠወለጉ፣ ሳይሠሩ በልጽገውና ሳይቀቡ ወዝተው እየተንደላቀቁ በመኖር ላይ ያሉት ወያኔወችና የእነሱ የጥፋት ዓላማ አስፈጻሚ ሆነው የተሰለፉት ከሀዲ ባንዳዎች ብቻ ናቸው።

ከዚህ ቀደም ያድናል ያሉት ኩል ዓይን አጠፋ በሚል ርዕስ አቅርቤ በነበረው ማሳሰቢያ "***አገር በማጥፋት በከበሩትና ችግር በመፍጠር በተካኑት በወያኔወችም ዘመን እንደ ሞት ያለመድነው ግን በየወሩና በየዓመቱ ብቻም ሳይሆን በየእለቱ ማለትም ይቻላል ህሊናን የሚያቆስልና አንጀትን አሳርሮ የሚያኮማትር ቀጣይ ችግር አሳጥተውን አያውቅም***" የሚል አባባል ነበረበት። ይኸውና ከዚያ ወዲህ ደግሞ በተከታታይ ያቀረቡልን ተመሳሳይ የችግር መስተንግዶዎች፣ የወጣቱ ከያኔ ወንድማችን ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ የጀግናዋ እህታችን ወ/ት ብርቱካን ሚዲቅሳና የሌሎችም ኢትዮጵያውያን በግፍ መታሰር፣ የአገሪቱ ወጣት ዜጎች የቃል-ኪዳን ጌቶቻቸው ዓላማ ማስፈጸሚያ ሆነው ወድሱማሊያ ተልከው ከገዛብን የጠላትነት ቂም በቀል



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በተጨማሪ ለአሳፋሪ ውርደትና ለአስከፊ እልቂት መዳረጋቸው፤ በግብርና ክፍለ-ኢኮኖሚ በምትታወቀው አገራችን የምግብ እህል ገብያ ላይ ጠፍቶ እንደ ሞት መድሀኒት ከሺህ ብር በላይ መሸጡና ሕዝቡ ከረሀብ ጋር ጦርነት ገጥሞ በማለቅ ላይ መሆኑ ወዘተ የአባባሌን ትክክለኛነት የሚያረጋግጡልኝ ይመስለኛል። ሰሞኑን ደግሞ ከፈጣሪው  የታደለውን አንደበቱን በሰው ሰራሽ ሕግ (ያውም በደመኛ ጠላቶቹ በታወጀ) ጨርሶ ለማፈን አቅደው "የእኔን ዓይተህ ተቀጣ" ዓይነት እርምጃ ከመውሰድ ጀምሮ የአንዲት እናት አገር ልጆቹ በሐይማኖት ምክንያት እርስ በእርሳቸው ሲተላለቁ በማየት ለመፈንደቅ የሚያስችላቸውን መርዝ በትነውና እሳቱን አቀጣጥለው  ውጤቱን በጉጉት እየተጠባበቁ ነው። በጽኑዕ የምተማመነውና የምመካው ግን ትዕግስተ-ሰፊና በተፈተነባቸው ፈተናዎች ሁሉ ወድቆ የማያውቀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትላንት በጎሳ ፖለቲካ ለማጫረስ ያቀረቡለትን በወገን ደም የተበከለ ድግስ እርሜ ነው ብሎ እንደ ደፋባቸው ሁሉ፣ ዛሬም ያን በቀላሉ የማይደፈርስ ኢትዮጵያዊ ህላፌነቱን በዳግማዊ ድል አድራጊት እንደሚያድሰው ነው።

ወደነጥቡ ለመመለስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እነዚህም ሁሉ እየሆኑበት የፈጠረው አምላክ በሰጠው የመንፈስ ጽናት እየታገዘ ጠላቶቹን አንበርክኮ በመጣል ነጻነቱን ለማስከበር የሚችልባቸው አጋጣሚወች እስከ ሚገጣጠሙለት ድረስ ችሎአቸው እየኖረ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን የማይቻል ሆኖ የቀረበለት የመጨረሻው ከባድ ፈተና የባህር በሯን እየዘጉና ዳር ደንበሩዋን እያስወረሩ መሄድ አልበቃንም ብለው አገሪቱን በመላ እንደ ቅርጫ ስጋ እየቆራረጡ ሽጠው ለመጨረስና ህልውናዋን ጨርሶ ለማሳጣት የጀመሩትን ዘመቻ በሰፊው መቀጠላቸውን ነው።

እንደሚታወቀው የታሪካዊ ጠላቶቻችን እስትራተጅካዊ ግብ አባይን ከምንጬ መቆጣጠር ነው። በዚህ ላይ ተመሥርተው ባልፉት ዘመናት ብዙ እርምጃዎችን ደረጃ በደረጃ ሲወስዱ መኖራቸውን የሚያረጋግጡ መረጃወችን መጥቀስ ይቻላል። ከነዚህም አንዱ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ለማዳን ክርስቲያኖች ወደ ኢየሩሳሌም፣ እስላሞች ደግሞ ወደ መካና መዲና እንደ ሚጎርፉት ሁሉ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና ሕዝቡዋን በዘርና በሃይማኖት ወዘተ እየከፋፈሉ ለማዳከም ቅጥረኛ ሆነው የሚነሱ መርገምቶች ሁሉ ሄደው የሚመሸጉት፣ ተዘርተው የሚበቅሉበት፣ ተኮትኩተው የሚያድጉበትና ተደራጅተው የሚዘምቱበት አመች ሁኔታዎች በጠላቶቻችን አገር የሚጠብቃቸው መሆኑን ስለሚያውቁ ነው። ሻቢያ-ወያኔወችና ግብረ-አጋሮቻቸው ሁሉ እነግብጽን የመሰሉ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ሤራ ውጤቶች መሆናቸውን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም። የግብጽ መሪዎች ደግሞ ለሕዝባቸው የመመረጫ ማጫ አድርገው ከሚያቀርቡዋቸው አንዱም "አባይ ቢገደብ የአባይን ያህል ደም ይፈሳል" ወዘተ የሚለው ዛቻነው። ይህ ዛቻ እንደቁራን የሚያመልኩበት ቋሚ መፈክራቸው ከሆነ ብዙ ምዕት ዓመታትን አስቆጥሯል። ይህ ሁሉ ድንፋታና ሤራ ግን በአሁኑ ትውልድ እንጅ በትላንቶቹ ጀግኖች ዘመን ከዛቻነቱ አልፎ ብዙም የሚያሰጋ አልነበረም። ምክንያቱም የትናንትናዎቹ አባቶቻችን የእናት ሀገርን ዳር ድንበር ማስጠበቁንና ለሀገር መሰዋቱን አሳምረው ያውቁበት ነበርና! የአሁኑ ትውልድ ግን ከእርግማንም ይባል ከትውልድ ዝቅጠት (የባህሪ ድህነቱንና የባእድ ምርኮኝነቱን ጨምሮ) ከራሱ አኩሪ ታሪክ ከመማርና የጀግኖች አባቶቹን ወኔ ከመውረስ ይልቅ የሌሎችን (በተለይም የጠላቶቻችንን) ታሪክ እየቀላወጠ ማወደስ ስለሚቀናው ትኩረት ሰጥቶ ያላጤናቸው ብዙ ቁም ነገሮች እየደበዘዙ በመሄድ ላይ ናቸው። ከእነዚህም አንዱ እነዚያ በእውነት ሰው ሆነው ሰወች የሚኖሩባት ታሪካዊት አገር አሰኝተዋት የኖሩት ጀግኖች አባቶቻችን ከአባይ ጋር ተዛምዶ ሊመጣ የሚችለውን ባለብዙ መዘዝ ችግር በሚመለከት አስቀድመው ስጥተውን ያለፉት ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነው። እሱም፦

“ካይሮ ድረስ ሄዶ ምንድነው ቅልውጡ፣

ግብጾች ለአበሻ ደግሰው ላይሰጡ” ያሉት ነበር። እኛ ግን ግብጾች ለኛ ለአባይና ጣና ጌቶች ምን እየደገሱልን እንደሆኑ እያወቅን በረጅሙ ያነጣጠሩብንን ለመከላከልም ሆነ



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሚሰነዝሩብንን ለመመከት የሚያስችል አንድም ዝግጅት ሳይኖረን ብዙ ዘመናትን በማሳለፋችን ይኸውና ከዛሬው ፈታኝ ችግር ላይ እንድንወድቅ ተገደናል። መቸውንም ቢሆን ደግሰው ሰጥተውን የማያውቁት ጠላቶቻችን ግን አንጸው በአሳደጉዋቸውና በስመ-ስምና ቀለም ኳኩለው በአመሳሰሉዋቸው የዘመኑ የፈርአን አምባሳደሮችና የእስክንድርያ ጳጳስ እንደራሴወች አማካይነት አገራችንን ያለምንም መድህንና ድርድር ሰጭና ተቀባይ ሆነው እየተረካከቡዋት ነው። እዚህ ላይ አብሮ ማገናዘብ የሚገባው ዋናዋን የእናት አገር አካል ለማስገንጠል 60000 አስገንጣይ ጦር አዝምተው ተዋግተው እንዳላስገነጠሏት ሁሉ የሀብታም አውድማ ለማታህል ባድሜ ለተባለች መንደር ግን የእናት አገርህ ሉዐላዊነት ተደፈረ በሚል ሽፋን (የትግራይ ክልል ስለሆነ ብቻ ማለት ነው) እንደ ብረት ለበስ ተሽከርካሪ የፈንጅ መጥረጊያ ሆነው ከ100000 ያላነሱ የአገሪቱ ዜጎች እንዲያልቁ መደረጉን ነው። ጦርነቱ የአገሪቱ ሉዐላዊነት ማስከበሪያ ሳይሆን የዜጎቿ ማስጨረሻ እንዲሆን ታስቦ የተደረገ መሆኑን ከሚያረጋግጡት አንዱም የአልጀርስ ስምምነት በሚል ሽፋን ያ ሁሉ መስዋዕትነት የተከፈለባት ባድሜ ብቻም ሳትሆን እንዲያውም በሌሎቸም አካቢቢዎች ተጨማሪ መሬት እየከለሉ ለመስጠት መዘጋጀታቸው ነው።

በሀገር ሉዐላዊነት ስም በባድሜ ጦርነት ላይ በመቶ ሺህ የሚቆጠር ወጣት ያስጨፈጨፉት ወያኔዎች በኢኮኖሚ ጠቀሜታው፣ በስትራቴጅካዊ አቀማመጡ፣ በታሪኩ፣ በቆዳ ስፋቱና በላዩ ላይ የሰፈረው ሕዝብ ብዛት ከባድሜ ጋር ሲዎዳደር በእጅጉ የሚበልጠውን ከሁመራ እስከ ጋመቤላ ሱዳንን የሚያዋስነውን 1600ኪ.ሚ የሚደርስ አጅግ ለምና በማዕድን የበለፀገ መሬታችን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ደብቅው ለሱዳን ለመስጠጥ ዝግጅቱን አጠናቅቀዋል። ወያኔወች ሁለንተናዊ ድጋፍ እየሰጡ ከዚህ ደረጃ ላይ ላደረሷቸው የአባይና ጣና ምንጭ ተስፈኞች ውለታ መመለሻ በረከት አድርገው ለመስጠት ለአቀዱት መሬት የማስመሰያ ሺፋን የሰጡት ሻለቃ ግዌን የተባለ የእንግሊዝ ወታደር በዚያ አልፎዋል ብሎው ነው። እውነታው ግን የጠላቶቻችን እስትራተጅካዊ ግብ ለሆኑት (ለጊዎን ምንጭና ለጣና ሕይቅ) የመሸጋገሪያ ድልድይ ለመስጠትና ለሚቀራቸው እርምጃ ቅድመ-ሁኔታወችን ለማመቻቸት ታቅዶ የተደረገ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

በመሠረቱ "ዳሩ ሲፈታ ማህሉ ዳር ይሆናል" እንደሚባለው የአገራችን ታሪካዊ የአስተዳደር ወሰን እንደ ባህር ዳር መሬት እየተሸረሸረ መወሰድ የተጀመረው በአሁኑ ወቅት ብቻም ሳይሆን መልካ-ምድረዊ አቀማመጧ፣ የተፈጥሮ ሀብቷና የረጅም ዘመናት ታሪኳ የገዛብት ጠላቶቿ ዙሪያዋን ከብበው እንደ ሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች በቅኝ ግዛት ለመግዛት ከዘመቱበት ዘመን ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል። ፊት ለፊት የቃጡት ተዋርደው ቢመለሱም ጥለውት የሚሄዱት ችግር ግን በየጊዜው እያመረቀዘ የእድሜ ልክ በሽታ በመሆን ለግዛቷ መሸራረፍ፣ ለሰላሟ መናጋትና ለእድገቷ መቆርቆዝ መሠረታዊ ችግር ሆኖ ኑሮዋል። በአሁን ወቅት ትውልድን ፈታኝ ሆኖ የቀረበውን ይህን የምራቡን ወሰን በሚመለከት የተጋረጠውን ችግር ገባ ብለን ብናይ እንኳ እስክ አሁን ትውልድ ያልተካቸው አጼ ቴዎድሮስ የተወለዱበት፣ ከክብራቸው ይልቅ ለዳር ደንበራቸው አንገታቸውን የሰጡት አጼ ዮሐንስ የተሰውበት ታሪካዊ ወሰን ነው። ከዚህም በተጨማሪ አጼ ምኒልክ ሱዳንን በቅኝ ግዛት ሲገዙ ከነበሩት እንግሊዞች ጋር የሁለቱን አገሮች ወሰን በሚመለከት የተደራደሩት የኢትዮጵያ ወሰን ገዳሪፍ ከሚባለው ከተማ ድረስ ስለሆነ ያ ሁሉ እንዲመለስላቸው ነበር። ነገር ግን በወቅቱ የነበረው የኃይል ሚዛን ስለአልፈቀደላቸው አደራውን ለተተኪው ባለአደራ - ለአሁኑ ትውልድ ሰጥተውት አልፈው ነበር።

ባለፈው ሱዳን ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ እናት ሀገርን ለመታደግ ከመሰል የትግል ጓዶቼ ጋር አቋቁመነው ከነበረው ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አርበኞች አንድነት የኅብረት ግንባር (ኢ.ዴአአኅግ) መሠረታዊ ዓላማወች አንዱ *"እናት አገር ኢትዮጵያን ለጥንታዊ ታሪኳ፣ ስምና ክብረ-ወሰንዋ ማብቃት"* የሚል ይገኝበት ነበር። ይኸም ማለት ዙሪያዋን ከበዋት የነበሩት ቅኝ ገዥወች



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በቅኝ ለሚገዟቸው አገሮች ማስፋፊያ አድርገው እየቆራረጡ የወሰዱባትን መሬቶች በማስመለስ ላይ ያነጣጠረ እንጅ ወታደሮቻቸው የረገጡትን መሬት ሁሉ አሳልፎ የሚሰጥ ቀርቶ በአጋጣሚ በእጃቸው ላስገቡት እንኳ ህጋዊ እውቅና ሰጥቶ የሚያጸድቅ አልነበረም። በአለመታደል ልበለውና ኢዴአአጎግ ፊት ለፊት ሊፋለማቸው ከተዘጋጀላቸው ደመኛ ጠላቶች ይልቅ በአገርና በወገን ስም ሲነግዱ በኖሩ ልማደኛ ወገን መሰል ጠላቶች በተደረገበት ርብርቦሽ ዓላማውን ከግብ ሳያደርስ ገና በለጋነቱ ጠውልጎ በመቅረቱ በእጅጉ አዝናለሁ።

አውጭ ይመስል የመቃብር ድመም እየፈነቀሉ የጀግኖችን አጽም ለማፍለስና አኩሪ ታሪካችንን ለማርከስ የዘመቱት አደራ-በሎች ግን የጥንቱን ዳር ደንበር ለማስከበር የሚጥሩና የሚግሩ ሳይሆን ወገኖቻችንን ለመውረር ወሰናችንን ጥሰው ያለፉትን ጠላቶቻችንን እንኳ ለኛ ጥሩ ሰውች ስለሆኑ አትቃወሟቸው እያሉ የሚመሰክሩና እንዲያውም ይኸ ይቀራቸዋል ብለው ቀድመው እያለፉ የሚያስረክቡ መሆናቸውን በገሀድ እያየን ነው። ድንቄም ኢትዮጵያዊ የሚያሰኘውም እንዲህ ያለው የዘመኑ ዮዲት ጉዶች ድርጊት ደጋግሞ መታየቱ ነው።

ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት አግጥጦ የቀረበልን ፈተና የአገር ህልውና ጥያቄ አጠያያቂ ደረጃ ላይ መድረስ ብቻም ሳይሆን ሰው ሆኖ ተፈጥሮ እንደ ሰው ያለመቆጠር ጥያቄንም አጣምሮ የያዘ መሆኑም ነው። ያልተዎቃች ክምሩን በዋስትና እያሳየ ተበድሮ ሲበላ የኖረ ባለ እዳ ከእለታት አንድ ቀን ልብ ገዝቶ በተበደረውና ክምሯን ቢወቃ አገኝባታለሁ ብሎ በገመተው መካከል ያለውን ልዩነት ሲያሰላ የተበደረው እዳ በልጦ ስላገኘው “አይ አንች ክምር ሲያዩሽ ያለሽ ትመስያለሽ እንጅ ተበልተሽ አልቀሻል” አለ ይባላል። እኛም ከስምና ካርታዋ ባለፈ የምናዝባት መሆኑዋ ቀርቶ እንደዜግነታችን በተራ ዜግነት እንኳ ለመኖር ባልቻልንበት አገርና በማናገኘው ስልጣን እንራኮታለን እንጅ የሚነገድባትም ትሁን የሕይወት መስዋዕትነት የሚካፈልባት እናት አገር ግን ዳር ድንበሩዋ ብቻም ሳይሆን ማህል አካሏ ሁሉ ሳይቀር ውስጥ ውስጧን እየተበለተች ተሸጣ የማለቋን መርዶ ከሰማን ውሎ አድሮዋል። ሰው ሆኖ ተፈጥሮ እንድ ሰው ያለመቆጠሩ ድፍረትና ውርደት የጀመረውም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው። እኛ ግን አንድ አድርጎ ሊያሳየን የሚችለውን ዓይነ-ልቦናችንን ስለአወረብንም ይሁን፣ አስተቃቅፎ ሊያሰልፈን የሚችለውን ፍቅር ስለነሳን ይመስለኛል፤ ነውም፤ እንዲህ ባለው እጅግ አሳሳቢ የህልውና ጥያቄ ላይ ከመረባረብ ይልቅ ቅድሚያ ሰጥቶ መዝመቱ የሚቀናንና መጪጪሁ የሚያጓጓን በትግል አጋራችን ላይ እየዘምትን መነካከሱና መራከሱ ላይ ነው። ይህን ችግር በሚመለከት  በገባኝ መጠን ሰፋ አድርጎ ለማሳየት በሌላ ጊዜ እመለስበታለሁ።

የወቅቱ ፈታኝ ችግር ወደሆነው ወደ ድንበሩ ጉዳይ ልመለስና በአሁኑ ወቅት የአካባቢው ነዋሪዎች እትብታቸው ከተቀበረበት ባድማቸውና ተወልደው ካደጉበት መንደራቸው፣ ከከብቶቻቸው ማሰማሪያ መስካቸውና ከውሀ መቅጃ ወንዞቻቸው እንዳይደርሱ ሰጭና ተቀባይ በሆኑት ጣምራ ጠላቶቻቸው ተከልክለው ምን ያህል እንደሚሰቃዩ የማይከታትል ካለ ለአገሩ ባእዳ፣ ለችግሩ እንግዳ የሆነ ስመ ኢትዮጵያዊ እብን መሆን አለበት። ስለሆነም የወደፊቱ ትግላችን የግዌንን ኮቴ መለካካት ሳይሆን ጥንታዊ ወሰናችንን የሚያዘክርና በዚያም ላይ ያነጣጠረ መሆን እንዳለበት በዚህ አጋጣሚ በብርቱ ማሳሰብ እወዳለሁ።

መልዕክቴን የማጠቃልለው እንደ ፖለቲከኞቹ እናት አገሩን በሰው - ፈጠር ድርጅት ለማይለውጠውና እሱ እራሱ በራሱ ላይ ድብብቆሽ መጫወትን ላልለመደው እውነተኛ የአገሪቱ ጌታ ለሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋሜ ጥሪ በማቅረብ ነው።



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ዕድሜ ሁሉን የሚያሳይ መስታወት ነው እንደሚባለው፣ 18 ዓመት ሙሉ ምን አገኘሁ? ምንስ አጣሁ? ወደፊትስ ምን ይጠብቀኛል? እያልክ አዘውትረህ እንድምታብሰለስል ደህና አድርጌ አውቃለሁ። እንዲህ ያለው ማብሰልሰል ለጎሊናዊ ዝግጅት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ቢኖረውም ወደ ተግባራዊ እርምጃ እስካልተለወጠ ድረስ ግን ማብሰልሰል ብቻውን የሚያሰለስል በሽታ ሆኖ ሁለመናህን ሊያዳክምብህና ሊጎዳህ እንደሚችል አብረህ ልታገናዝበው ይገባል። ስለጠላቶችህ ደመኛ ጠላትነት ሌላ ነጋሪ ሳትፈልግ አንተው እራስህ በሁለንተናዊ ዕምነትና ግብራቸው ደህና አድርገህ አውቀህቸዋል። ለአንተ የዘመናት ታሪክ ያስተሳሰረውና የአገር ልጅነት ፍቅር ያስተቃቀፈው ዝምድና ቀርቶ ከሰባዊነት አመለካከት አኳያ እንኳ እንደማያዝኑልህ በብዙ ለህሊና በሚከብዱ ዘግናኝ ድርጊቶቻቸው ያረጋገጥህ ይመስለኛል። ከአንተ ይልቅ ለአንተ ታሪካዊ ጠላቶች ፍቅራቸው የደራና ዕምነታቸው የጸና ነው። ትላንት ከጎንህ የነበሩት ወንድምህና ጎረቤትህ ዛሬ የሉም። አንድም ተገለዋል ወይም በጨለማ እሥር ቤት ታጉረው የመሞቻ ቀናቸውን የሚጠባበቁ ናቸው። ከእንደዚህ ያለው መቅሰፍት አምልጠው ለስደት የበቁት ደግሞ ዕድለኞች ናቸው የሚባሉ ሆነዋል። (በክብር ተወልደው በእንክብካቤ ካደጉባትና ለውግ ለማእረግ ከበቁባት እናት አገር ተንቅሎ መሰደድም  እንደ መልካም ዕድል ተቆጥሮ ማለት ነው።) እንግዲህ የጊዜ ጉዳይና የቀን ቆጠራ ካልሆነ በስተቀር የሚቀጥለው ተራ የአንተ መሆኑን የምታጣው አይመስለኝም።

ትላንት ሞቆና ደምቆ የነበረው ቤትህ፣ መደላደል ጀምሮ የነበረው ኑሮህና በመረጋጋት ላይ የነበረው ሰላምህ ዛሬ ግን ምስቅልቅላቸው ወጥቶ ታውከዋል። ለልጆችህ የምታጎርሰውና የምታለብሰው አጥተህ ምን ያህል እንደምትጨነቅ እንደ አንተው በችግሩ ዱላ የሚደበደብና በእሳቱ ወላፈን የሚገረፍ ካልሆነ በስተቀር ይህን ይመስላል ብሎ በቃላት ለመግለጽ በእጅጉ ይከብዳል። ለዘመናት በአስተሳሰረህ አብሮነት ሀዘንና ደስታውን እየተጋራህ የኖርክበትን የወንድማማችነትና የእህትማማችነት ፍቅር ገለው በመቅበር ጥላቻና ጠላትነትን ሊያንግሡልህ ሌት ተቀን እየጣሩ ናቸው። እንዲያውም የአንተ ሰፊ ትእግሥትና ኢትዮጵያዊ ሀላፊነት ባይከላከላቸው ኑሮ አንግሠው በጥቁር ደም የተበከለ ዘውድ ሊጭኑልህ አዘጋጅተው ነበር። ብሔራዊ አመለካከትክን ከማደብዘዝም አልፈው ገሎ መቅበር የዓላማቸው አካል በመሆኑ የሌለብህን ጥላሸት እየቀቡ መንደርተኝነትን እንድትላበስ ቀን ተሌት እየጣሩ ነው። በአጠቃላይ ከመንደር ታዛ አልፎ ማሰብና ተገላምጦ ማየት የማይችለው የጠባብ አዕምሮዋቸው አቅም አልፈቅድላቸው ብሎ እንጅ የሚችሉ ቢሆን ኖሮ ፀሀይዋን አጥፈተው፣ የምትተነፍሰውን አየር አቁመውና ወራጅ ወንዞችን ሁሉ አድርቀው በአንድ ጊዜ ቢጨርሱህ በእጅጉ ደስ ባላቸው ነበር።

ገሀድ እውነታው የሚያሳይህ ይህን ከሆነ ለአንተ የጨርሶ መጥፊያ ለጠላቶችህ ደግም የጨርሶ ማጥፊያ ዕድሜና ጊዜ የምትሰጣቸው ለምንድን ነው? በአንድ ወቅት ***"ሁልጊዜ እንዳይመርርህ ከፈለግህ ለተወሰነ ጊዜ እራስህን ወደመራራነት ለውጠው"*** ብዬ ማሳሰቤን አስታውሳለሁ። ዛሬም ደግሜ የማቀርብልህ ጥያቄ ያንኑ ነው። አጠንክሬ ይህን የምለው መርሮህና አምርረህ ከተነሳህ የጠላቶችህን የአሺዋ ክምር በቀላሉ ለመናድና የሚይዙትንና የሚጥሉትን አሳጥተህ በወጡበት ለማስቀረት የሚያስችል ኃይልና ወኔ እንዳለህ ስለማውቅ ነው።

እንደሚገባኝ ሁለት ከግንዛቤ ጋር የተያያዙ ችግሮች ያሉ ይመስለኛል። የመጀመሪያው በወያኔወች ፕሮፓጋንዳ የመሰለብ ችግር ነው። በእርግጥ በምን ኃይልና ችሎታ ተጠቅመው ከዚህ ደረጃ ደረሱ ለሚለው ጥያቄ በጥልቀት ካላወቁ ብዙ መደነጋገር ሊፈጥር ይችላል። ፈጥሯልም። በአሁኑ ወቅት ላሳይህ የምፈልገው ግን ዕውነተኛ ታሪካቸውን ነው። በአገራችን የመሞቻዋን ቀን የማታልፍ አውሬ ገዳይዋን ታስመሰግናለች



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

የሚባል ትምህርት ሰጭ አባባል አለ። የወያኔወችም የሌላቸውን ስምና ጀግንነት አገኘን የሚሉት በሁለት ወቅቱ በአገጣጠማቸው ችግሮች ታግዘው መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የመጀመሪያው ደጋፊ ችግር በብዙ ቅራኔና ችግር ተተብትቦ ተይዞ የነበረውን ደርግ ለመገልበጥ ፀረ-ደርግ አቋም በነበራቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ይካሄድ የነበረው ርብርቦሽ ነበር። በእርግጥ የወቅቱ ትግል አስፈላጊነት ባያጠያይቅም ደርግን ገልብጥው ሥልጣኑን ተሻምተው ለመጨበጥ ሲራወጡ የነበሩት ድርጅቶች ግን እንድቁራ ከመጯጯህና ተተኪውን ወጣት ትውልድ እንደገና ዳቦ ማህል አስገብተው አብረው ከማቃጠል ባለፈ የፈየዱት አንድም ሕዝብ ጠቀም ነገር አልነበረም። ይራወጡለት ለነበረው ሥልጣን የሚያበቃ ዝግጁነት እንዳልነበራቸውም ከደርግ ውድቀት በኋላ የታየባቸው ዕድገትና ለውጥ የለሽ የኤሊ ጉዞ ያረጋገጠው ሐቅ ይመስለኛል። በዚህ ችግር ምክንያት በተፈጠረው ክፍተት ወያኔወች እንደ አይጥ ሾልከው ለመግባትና በቀላሉ ወደ ስልጣን ለመንጠላጠል አመች ሁኔታዎች ሊፈጠሩላቸው በመቻሉ ነው።

ሁለተኛው መሠረታዊ ችግር ደግሞ ፊት ለፊት ዘምተው ድባቅ ተመትተው የተመለሱትና የውርደት ማቅ ደርበው እንዲኖሩ የተገደዱት ጠላቶቻችን እንደዚያ ያለውን በሀገር ውስጥ የተፈጠረ ቅራኔ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የዘመናት በቀላቸውን ለመወጣት ሲሉ ኢትዮጵያዊ ክብራቸውን ለቅጥረኛ ባርነት ሸጠው ለተገዙላቸው ሞራለ-ቢሶች በሰጧቸው ሁለተናዊ ድጋፍና በከፈሏቸው የሽያጭ ገንዘብ እነርሱም በተራቸው ከከሐዲ ባንዳወች ላይ እንደ ሸቀጥ ገዝተው ያገኙት ድል ነው። ከዚህ ውጭ እነሱ የሚሉት ታሪክና ታምር ፈጽሞ የለበትም። እንዲያውም በውጊያ በልጠንና በጀግንነት ልቀን ከሚሉ ይልቅ ተገድለን መቃብር ውስጥ ከገባን በኋላ አፈር የሚያለብሰን ስለአጣን ተመልሰን ወጥትን ከዚህ ደረጃ ላይ ደረስን ቢሉ ትክክለኛ ታሪካቸውን ይገልጻል። ወደኋላ ተመልሸ ይህን ሁሉ እንድገልጽልህ የተገደድኩት ህሊናህን የሚያዞርና ጀሮህን የሚያደነቁር በክህደት የተቀመመ ደረቅ ውሸት በየዕለቱ የሚያዘንቡብህ አንድ ቀን ገንፍለህ ብትነሳ ቆንጥጦ መያዝ የሚችል እግርና ሕዝባዊ አመጹን መክቶ ለማስቀረት የሚያስችል አቅም እንደሌላቸው ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው። ስለዚህ ሙክቱ የመታረጃው ወቅት ካለፈ በኋላ ቢታረድ ሥጋው ገንትሮ እንደማይበላ ሁሉ የአንተንም የድል ትንሣኤ መፈሰኪያ ቀን እያራዘምክ እንደ እነሱ በዕምነትህ ድህ፣ በሞራልህ የተሰለብክ ቀዝቀዛና በሕዝባዊ ጉልበትህ በራሱ መተማመን የሌለው ደካማ መስለህ ልትታያቸው አይገባም።

ሁለተኛው ከግንዛቤ ጋር የተያያዘው ችግር የአንተን የላቀ አገር አድን ሀላፊነት ኑና ውሰዱ ብለሀቸው ቀርቶ ብትወረውርላቸው እንኳ ፈጥነው ሊቀበሉህ በማይችሉና ቀድመው በማይሰለፉልህ ባህር ማዶ ኗሪ የምላስ ወዳጆች ላይ ዕምነትህን መጣልህ ነው። በእርግጥ የሀገር ጉዳይ፣ ያአገራቸን ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የሁሉም ዜጎች ጉዳይ መሆኑ ባያጠያይቅም፣ ህሉም የአገሪቱ ዜጎች ናቸው የተባሉት ሁሉ **እውነተኛ ዜጋ** ሆነው ባልተገኙበት በአሁኑ የዳግማዊ ይሁዳወች ዘመን ሕዝባዊ ሀላፊነትን ሊወጣ በማይችል ሌላ ኃይል ላይ ጥሎ ተከናንቦ መተኛት ትውልድና ታሪክ ይቅር የማይለው ስህተት ነው። የችግሩን ገፈት በግንባር ቀደምነት እየተጎነጨኸው ያለኸው አንተ እንደመሆንህ መጠን፣ አንተንም ሆነ እናት ሀገርህን ነፃ የምታወጣው አንተ ብቻ መሆንህን አውቀህና ከባህር ማዶ ማንንም ሳትጠብቅ ዛሬውኑ ልትነሳ ይገባሀል። ስለዚህ መሪ መፈክርህ “አገሩ ለባላገሩ በባለአገሩ” የሚል መሆን አለበት። ለእንደዚህ ያለው ሕዝባዊ ድል እንድትበቃ ከፈለግህ ደግሞ በማንኛውም ቦታና ጊዜ መገልገል የምትችልበትን አንተነትህንና የወንዝና ሸንተረርህ ማስከበሪያና የጎራህ መፋለሚያ ሊሆንህ የሚችለውን መሳሪያህን አዘጋጀው። መሳሪያ ሲባል ደግሞ የግድ ጠብመንጃ ብቻ መሆን አለበት ማለት አይደለም። እናት ከሚበጠብጥ ከንተሮ ጀምሮ ቆርጦ የሚጥለውና ሰንክሎ የሚያስቀምጠው ሁሉ መሳሪያህ መሆኑን መዘንጋት የለብህም። አንድ ቀን፡-



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

“ተሚሚቀ ገብይው እጅጉን ደምቀ፣

በጢት ይገበያል ሼሬታ ያወቀ።"

የሚል ሕዝባዊ ደወል የተመታ ዕለት ጋራና ሸንተረሩን ፈጥኖ በመቆጣጠር ገብያውን ማድመቅና ሸሬታውን ማሳመር የአንተ ሀላፊነትም፣ ግዳጅም ነው። በዕውነት እመነኝ ያን ያደረግህ ዕለት እነዚህ አይበገሬ መሳይ ጠላቶችህ ጥድፊያና እሩጫቸው ወደጎሬያቸው እንጅ ወደ አንተ ጎራ እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ።

<u>ልዑል እግዚአብሔር፤</u>

-የሰው ዘር ዳኛ ነውና ፍርድ አያሳጣን!

-አንድ የዕምነት ማተብ አሳስሮ፣ አንድ የዓላማ ቋንቋ አናግሮ፣ በአንዷት እናት አገር ፍቅር አስተቃቅፎ ሊያዘምተን የሚችል ልቦና ይስጠን!

-ጥቂቶች በመረረ ጥላቻ የሚያይዋትን፣ ለብዙሀኑ ግን መተኪያ የሌላት እናት የሆነችውን ሀገረ-እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ለዘላለም ይጠብቅልን! አሜን!



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com